ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**
www.KINIJIT.org

# ‹‹ቅንጅትን ለማፍረስ ያፈነገጠና የቅንጅት ፓርቲን ሕገ ደንብ የጣሰ በቅንጅት ስም ለመንቀሳቀስ የሕግም ሆነ የሞራል ብቃት የለውም››

*ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ*

የቅንጅት አመራሮች ከእስር ከተፈቱ በኋላ የቅንጅትን ፓርቲ ለማፍረስ ሲንቀሳቀሱ በነበሩ 5 የአመራር አባላት ላይ ከእንቅስቃሴያቸው እንዲታቀቡና በፓርቲው ስም ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳይሰጡ ለማድረግ የቅንጅት ፕሬዚዳንት ጊዜያዊ የእግድ ርምጃ መውሰዳቸው ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ የታገዱ የአመራር አባላት የታገዱበት ጉዳይ በላዕላይ ምክር ቤት አባላት ተጣርቶ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በትዕግስት ከመጠበቅ ይልቅ መሰሎቻቸውን በማሰባሰብ የመከፋፈሉን ሥራ አጠናክረው ቀጥለውበታል፡፡

የቅንጅት አመራር የሃሳብ ልዩነት ያስጨነቀው ሕዝባችን አትከፋፈሉ አንድ ሁኑ እያለ ድምፁን ከፍ አድርጐ እየጮኸና ሌሎችም ጉዳይ ያሳሰባቸው ኃይሎች ሁሉ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ አገር እየተንቀሳቀሱ ባሉበትና አስታራቂ ሽማግሌዎችም የተፈጠረውን ችግር በመፍታት የቅንጅት አመራሮች አንድ ሆነን ቅንጅትን እንድናጠናክር በከፍተኛ ድካምና ጥረት ላይ መሆናቸው እየታወቀ

1. በእነ ወ/ሪት ብርቱካን የሚመራው አፈንጋጭ ቡድን የሽማግሌዎቹንና የሕዝቡን ጥያቄ ወደጐን በመተው በተጓደሉ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አባላት ምትክ የአቶ ተመስገን ዘውዴ ቡድንንና ሌሎችንም ግለሰቦች በማሟላት የፓርቲያችንን ሕግና ደንብ በመጣስ የጠቅላላ ጉባኤውን ሥልጣን እየተጋፉ ይገኛሉ፡፡
2. ቅንጅት ለሌላ ቡድን በመሰጠቱ ምክንያት በፓርቲያችን ሕልውናና በምርጫ ምልክቱ ላይ ምን መደረግ አለበት? የሚለውን አጀንዳ ያለነው የላዕላይ ምክር ቤት አባላት አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በጋራ መምከርና የደረስንበትን ድምዳሜ ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ የመጨረሻ ውሳኔ ማሰጠት ተገቢው አካሄድ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የአፈንጋጭ ቡድኑ አባላት ከአቶ ተመስገን ዘውዴ ጋር የቡድንተኝነት ግምባር

በመፍጠር አዲስ ፓርቲ ለመመስረት መወሰናቸው ብዙ መስዋዕት የተከፈለበትን የቅንጅት ፓርቲን ስም ለማጥፋት ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል። ውሳኔያቸውም ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆነ እና የጠቅላላ ጉባኤውን ሥልጣንና መብት የተጋፋ ሆኖ አግኝተነዋል።

3. አሜሪካን አገር ለሥራ ጉብኝት የተላከው የልዑካን ቡድን አባላት አሜሪካ በነበሩበት ጊዜ የቅንጅትን ፕሬዚዳንት በማግለል የቅንጅትን አመራር ለመቀራመት ያደረጉት ሙከራ የከሸፈ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን ቀደም ሲል የነበራቸውን የሥልጣን ጥማት ዛሬ ደግሞ አዲስ ፓርቲ በመመሥረት ሰበብ እየተወጡት ይገኛሉ። እውነተኛውን የፓርቲ ሥልጣን ሊሰጥም ሆነ ሊነሳ የሚችለው አካል ግን ጠቅላላ ጉባኤው መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል።

4. አራት ፓርቲዎች ያቀረብነው የቅንጅት ውህደት ሰነድ ምርጫ ቦርድ አልቀበልም ባለበት ጊዜ እና እኛም እስር ቤት በገባንበት ወቅት እነ አቶ ተመስገን ዘውዴና እነ አቶ አየለ ጫሚሶ የቅንጅትን ፓርቲ በመካድ 1500 ፊርማ በማሰባሰብ ተለጣፊ ቅንጅት ማቋቋማቸው ይታወሳል። በወቅቱም ፓርላማ የገቡ የቅንጅት አባላትን በዲሲፕሊን ሲከሱና ከፓርቲ አባልነት ሲያባርሩ የቆዩ፣ ሲሆን ዛሬ ደግሞ በቅንጅት አመራሮች መካከል የተፈጠረውን ልዩነት ተጠቅመው በሌሎች የቅንጅት አመራር አባላት ተይዞ የነበረውን የአመራር ቦታ እነ ወይዘሪት ብርቱካን ዳረጐት ሊሰጣቸው እንደሆነ ከሚያደርጉት ስምምነት መረዳት ይቻላል። ግለሰቦቹ የመረጣቸው ሕዝብ ለቅንጅት አንድነት ያለውን ፍላጐት የረሱ በመሆናቸው የቅንጅት ስም ከእውነተኞቹ መሪዎች ነጥቀውና አስነጥቀው ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ ፓርቲ ፈጠርንልህ የሚሉበት የሕግም ሆነ የሞራል ብቃት የላቸውም።

5. ትላንት ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበት የቅንጅት ፓርቲ ስም ለሌላ በመስጠቱ በአመራሩና በአባላቱ ደረጃ በደረጃ ሊደረጉ የሚገባቸው የሕግና የዲፕሎማሲ እርምጃዎች ሳይወሰዱ ከቅንጅት ያፈነገጠው የአንጃ ቡድን አባላት አዲስ ፓርቲ ለመፍጠር መንቀሳቀሳቸው ተደብቆ የቆየውን አላማቸውን ይፋ ያወጡበት አጋጣሚና ‹‹ሁሉም በየፊናው ይሂድ›› የሚለውን የከፋፋዩን የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን

መፈክር ተግባራዊ እያደረጉ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲረዳልን በአንክሮ እንጠይቃለን።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምም በቅንጅት የአመራር አባላት መካከል የተፈጠረውን ልዩነት በመፍታትና በማስታረቅ ቅንጅት አንድ ሆኖ እንዲቀጥል የሽምግልና ተግባር ያከናውናሉ ተብሎ በብዙዎች ተጠብቆ ነበር። ነገር ግን እሳቸው አፈንጋጩን ቡድን ደግፈው ሌላውን አግለውና ነቅፈው በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ላይ ቃለ መጠይቅ መስጠታቸው ሕዝብን ያሳዘነ ክስተት ሆኗል። ይባስ ብለውም ከእነ ወ/ሪት ብርቱካን ጋር መቀላቀልንና በተጓደሉ የላዕላይ ምክር ቤት የማሟያ ምርጫ አንዱ ሆነው መቅረባቸውን በነፃ ፕሬሱ ላይ ስናይ በእጅጉ ተገርመናል። አንጃውን ቡድን አጠናክረው ለመሄድ የፈለጉ መሆኑን ሕዝብ እንዲያውቅልን እናሳስባለን። ቅንጅትን የማፈራረስና የመከፋፈል ተግባር እያከናወነ ያለውን የአንጃ ቡድን እያወገዝን መላው የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችም ከጐናችን እንድትቆሙ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ቅንጅት አንድ ነው

ጥር 2000 ዓ.ም

አዲስ አበባ